የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፮
አዲስ አበባ – ኅዳር ፴፩ ቀን ፲፱፻፺፫

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

7[th] Year No. 6
ADDIS ABABA– 30[th] November, 2000

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፳፬/፲፱፻፺፫ ዓ.ም
ለባለብዙ ዘርፍ የኤች·አይ·ቪ/ ኤድስ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ............. ገፅ ፩ሺ፬፻፴፭

## CONTENTS

Proclamation No. 224/2000
International Development Association Credit Agreement for Financing Multisectoral HIV/AIDS Projects Ratification Proclamation ........................................................ Page 1435

## አዋጅ ቁጥር ፪፻፳፬/፲፱፻፺፫

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለባለብዙ ዘርፍ የኤች·አይ·ቪ / ኤድስ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ኤስ·ዲ·አር· ፵፭ ሚሊዮን ፪፻ ሺህ (አርባ አምስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺህ ኤስ·ዲ·አር) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ·ኤ·አ· አክቶበር ፲፪ ቀን ፪ ሺህ በዋሽንግተን ዲ·ሲ· የተፈረመ በመሆኑ፣

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለም አቀፍ ውሎች ተፈጻሚ ከመሆ ናቸው በፊት መጽደቅ ስላለባቸው፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ኅዳር ፴፩ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ·ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ለባለብዙ ዘርፍ የኤች·አይ·ቪ/ ኤድስ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፳፬/፲፱፻፺፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 224/2000

### *A PROCLAMATION TO RATIFY THE DEVELOPMENT CREDIT AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION*

WHEREAS, a Development Credit Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Credit amount of SDR 45,200,000 (forty five million two hundred thousand Special Drawing Rights) for financing the Multisectoral HIV/AIDS Project, was signed in Washington D.C. on the 12[th] day of October, 2000;

WHEREAS, basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 30[th] day of November, 2000;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Credit Agreement for Financing Multisectoral HIV/AIDS Projects Ratification Proclamation No. 224/2000".

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O. Box 80,001

፪. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ አክቶበር ፲፪ ቀን ፪ ሺህ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. የተፈረመው ቁጥር ፫ሺህ፬፻፲፮–ኢ.ት. የብድር ስምምነት ነው።

፫. የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ኤስ.ዲ.አር ፵፭ ሚሊዮን ፪፻ ሺህ (አርባ አምስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከኅዳር ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ኅዳር ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation "Credit Agreement" means the Credit Agreement No. 3416–ET signed in Washington D.C. on the 12th day of October, 2000 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association.

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Credit amount of SDR 45,200,000 (forty five million two hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Credit Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 30th day of November, 2000.

Done at Addis Ababa, this 30th day of November, 2000.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE